# ለእግዚአብሔር ፍቅር

“ … እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።” (ኢሳ 48 ÷ 17)
God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. / E-mail – hello@ethiogodslove.org

ታሕሣስ 1996 Dec. 2003 “ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፤ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።” (ኢሳ 54÷13)
አዘጋጅ ፦ መላኩ ማሞ ትዕዛዙ

## ዓመተ ምሕረት

# ትንቢቱ÷ልደቱ÷ ዳግም ምጽዓቱ

“ሕፃን ተወልዶልናልና÷ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር÷ ኃያል አምላክ÷የዘላለም አባት÷የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።”
(ትንቢተ ኢሳይያስ 9÷6)



“የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች። እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ በስውር ሊተዋት አሰበ። እርሱ ግን ይህን ሲያስብ÷ እነሆ የጌታ መልዓክ በሕልም ታየው÷እንዲህም አለ፦ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ÷ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ልጅም ትወልዳለች፤እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።” (ማቴዎስ 1÷18-21)

“አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ÷ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መሐከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ። ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ÷ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል።” (ትንቢተ ሚክያስ 5÷2)

“ኢየሱስም፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ ÷ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው።” (የዮሐንስ ወንጌል 8÷58)

“እነሆ÷ ድንግል ትፀንሳለች÷ ወንድ ልጅም ትወልዳለች÷ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።”
(ትንቢተ ኢሳይያስ 7÷14)

“በመጀመሪያው ቃል ነበረ÷ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ÷ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።”
(የዮሐንስ ወንጌል 1÷1)

“ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ÷ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን።”
(የዮሐንስ ወንጌል 1÷14)

“ሰማይም ተከፍቶ አየሁ÷እነሆ አምባላይ ፈረስ÷ የተቀመጠበትም የታመነና እውነተኛ ይባላል÷በጽድቅም ይፈርዳል፤ ይዋጋልም። ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ናቸው÷በራሱ ላይም ብዙ ዘውዶች አሉ÷ ከእርሱም በቀር አንድ እንኳ የማያውቀው የተጻፈ ስም አለው፤ በደምም የተረጨ ልብስ ተጐናጽፎአል÷ ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል።”
(የዮሐንስ ራእይ 19÷11-13)

ጌታ ኢየሱስ ከሁለት ሺ ዓመት በፊት ሥጋ ለብሶ በሰውነት ቢወለድም÷“አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ” ነው። እግዚአብሔር ወልድ ሆኖ ያለ÷የነበረና ለዘለዘለም የሚኖር አምላክና ጌታ ነው። አሁንም በክብር ሊገለጥ አለው።

## ታኅሳስ 2003 ወይም 1996 ዓመተ ምሕረት

## መልካም የጌታችን የመድኃኒ ዓለም ልደት በዓል፡

## “መልአኩም እንዲህ አላቸው፡- እነሆ፥ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት፡ እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና።” … “ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን፡ ሰላምም በምድር፡ ለሰውም በጎ ፈቃድ፡” (የሉቃስ ወንጌል 2፥ 10-14)

የእግዚአብሔር ፍቅር ደብዳቤ አንባቢዎች!!

የዚህ ደብዳቤ አዘጋጅችና ቤተሰባችን፡-
መልካም የጌታ ልደት በዓልና መልካም አዲስ ዓመት
እንመኝላችኋለን። በእግዚአብሔር ፍቅር እንወዳችኋለን።



# ኢየሱስ ጌታ ነው።
# ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ።



# ከኖኅ መርከብ የተማርኩት

(ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 6ን ያንብቡ)

በሕይወቴ ዘመን ሁሉ የሚጠቅሙኝንና ከኖኅ መርከብ የቀሰምኳቸውን ትምሕርቶች ላካፍላችሁ:- 1ኛ፡ የደኅንነት መርከብ አያምልጥህ:: 2ኛ:- ለሁሉም የተዘጋጀው ማምለጫ አንዱ መርከብ ብቻ ነው:: 3ኛ፡ ኖኅ መርከቡን በሠራበት ወቅት ዝናቡ ገና አልጀመረም ነበረ:: ስለዚህ ሁሉም መዘጋጀት ይችሉ ነበረ:: 4ኛ:- የማይመች ጊዜ ሊመጣ ስለሚችል÷ ተዘጋጅተህ ኑር፤ከልክ አትለፍ:: 5ኛ:-ለተቺዎች በመበገር÷መደረግ ያለበትን መልካም ነገር ከማድረግ አትቆጠብ:: 6ኛ:- ዞሮ መግቢያህ በጎርፍ እንዳይወሰድ አስቀድመህ ቤትህን በከፍታ ቦታ ላይ ሥራ:: 7ኛ:- ጎርፉ ካለፈ በኋላ ለመርባት እንድትችል ተባትና እንስት ሁን:: 8ኛ፡ ፈጣንነት ሁል ጊዜ ያስቀድማል ብልህ አትሳት:: ምክንያቱም በኖኅ መርከብ ውስጥ ከነበሩት ሁለት ፈጣን ጥንቸሎች ጋራ ሁለት ዔሊዎችም ነበሩ:: ዔሊ አይፈጥንም::

9ኛ:- የመከራ ጎርፍ ሊውጥህ በሚመጣበት ጊዜ እስኪያልፍ ድረስ በትዕግሥት ለመንሳፈፍ ዝግጁ ሁን:: 10ኛ:- የሰውን ዘር ከጥፋት ያተረፈው የኖኅ መርከብ የተሠራው እግዚአብሔርን በታዘዘ ተራ ሰው፡ በኖኅ ሲሆን:- ብዙ ሕዝብ ይዞ የሰመጠው ታሪካዊው:- ታይታኒክ የተባለው መርክብ ግን፡ በመርከብ ሥራ ጠቢባን የተሠራ መሆኑን አስተውል:: 11ኛ፡ የጥፋት ውኃ የቱንም ያክል አስፈሪ ሆኖ ቢታይና÷ተስፋ በቅርብ ባይታይህም እንኳ÷ከእግዚአብሔር ጋር ከሆንህ:- የተስፋው ቀስተ ዳመና ከአድማስ ባሻገር መኖሩን አትጠራጠር:: 12ኛ:- ብታምንም÷ ባታምንም÷ እግዚአብሔር የተናገረው ሁሉ ÷ እንደ ቃሉ ይሆናል:: ምክንያቱም "ሰማይና ምድር ያልፋሉ ÷ ቃሌ ግን አያልፍም::" ተብሎ ተጽፎአል:: (የማቴዎስ ወንጌል 24÷35)

ኖኅ እግዚአብሔር የተናገረውን አምኖ መርከብ በመሥራቱ÷ ከቤተ ሰቡና ከምድር ፍጥረት ሁለት ሁለት ዘርን ይዞ ከጥፋት ውኃ ተረፈ:: (ዘፍጥረት 6::) "ኖኅ ገና ስለማይታየው ነገር ተረድቶ እግዚአብሔርን እየፈራ ቤተ ሰዎቹን ለማዳን መርከብን በዕምነት አዘጋጀ÷በዚህም ዓለምን ኰነነ÷በዕምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ::" (ዕብራ ውያን 11÷7)

## ለመሆኑ በኖኅ ዘመን እንደነበረው የጥፋት ውኃ ዳግመኛ ይሆናል?

አይሆንም:: ምክንያቱም:- "... ከዚህ ቀደም እንዳደረግሁት ሕያዋንን ሁሉ እንደገና አልመታም::" ተብሎ ተጽፎአል:: (ኦሪት ዘፍጥረት 8÷21)

## በዚህ ዘመን እግዚአብሔርን የማያመልኩት ሰዎች እንዴት ይቀጣሉ?

በእሳት ነው:: ይህች ዓለምና ጌታ ኢየሱስን የማያመልኩት ሁሉ እሳት ይጠብቃቸዋል:: መጽሐፍ እንዲህ ይላል::

"...በመጨረሻዎቹ ቀኖች የሚያፌዙና ክፉ ምኞታቸውን የሚከተሉ ዘባኞች ይመጣሉ፤ እነርሱ "ጌታ ኢየሱስ ይመጣል ተብሎ ተስፋ ተሰጥቶ አልነበረምን? ታዲያ የት አለ? የቀድሞ አባቶቻችን ከሞቱበት ጊዜ አንሥቶ ሁሉ ነገር ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እንደ ነበረ ነው" ይላሉ::እነዚህ ሰዎች ከብዙ ጊዜ በፊት ሰማይና ምድር በእግዚአብሔር ቃል መፈጠራቸውን ሆን ብለው "አናውቅም" ይላሉ፤ ምድርም የተሠራችው ከውኃና በውኃ መሆኑን ይክዳሉ:: በዚያን ጊዜ የነበረውም ዓለም በውኃ ተጥለቅልቆ ጠፋ

<u>አሁን ያሉትም ሰማይና ምድር÷ዐመፀኞች ሰዎች እስከሚጠፉበት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ በዚሁ በእግዚአብሔረ ቃል ለእሳት ተጠብቀው ይኖራሉ::</u>

... አንዳንድ ሰዎች እንደሚመስላቸው ጌታ ኢየሱስ የተናገረውን የተስፋ ቃል ለመፈጸም አይዘገይም፤ ነገር ግን ሰው ሁሉ ለንስሓ እንዲበቃ እንጂ ማንም ሰው እንዳይጠፋ ፈልጎ ስለ እናንተ ይታገሣል:: <u>የጌታ ቀን እንደ ሌባ በድንገት ይመጣል</u>፤ በዚያን ቀን ሰማይ በታላቅ ድምፅ ያልፋል፤ <u>ፍጥረት ሁሉ በእሳት ተቃጥሎ ይጠፋል::</u> <u>*ምድርና በእርስዋ ላይ ያለው ነገር ሁሉ ይቃጠላል*</u>፤ እንግዲህ ሁሉ ነገር በዚህ ሁኔታ የሚጠፋ ከሆነ÷ታዲያ እናንተ በቅድስናና በመንፈሳዊነት ኑሮ መኖር እንዴት አይገባችሁም! ... እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት በናፍቆት የምትጠባበቁና በቶሎም እንዲመጣ የምትሠሩ ሁኑ፤ ... <u>*በዚያን ቀን ሰማይ በእሳት ተቃጥሎ ይጠፋል*</u>፤ ፍጥረቶችም በእሳት ግለት ይቀልጣሉ፤ ነገር ግን እኛ ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር በተስፋ ቃሉ መሠረት እንጠባበቃለን::" (2 ጴጥሮስ 3÷ 3-13 አዲሱ ትርጉም)

ስለዚያች፡ቀንና፡ስለዚያች፡ሰዓት፡ግን፡ከአባት፡ብቻ፡በቀር፡የሰማይ፡መላዕክትም፡ቢሆኑ፡ልጅም፡ቢሆን፡የሚያውቅ፡የለም::የኖኅ ዘመን፡እንደ፡ነበረ፡የሰው፡ልጅ፡መምጣት፡ እንዲሁ፡ይሆናልና:: በዚያች፡ወራት፡ከጥፋት፡ውኃ፡በፊት÷ኖኅ፡ወደ፡መርከብ፡እስከ ገባበት፡ቀን፡ድረስ፡ሲበሉና፡ሲጠጡ፡ሲያገቡና፡ሲጋቡም፡እንደ፡ነበሩ÷ የጥፋት፡ውኃም፡መጥቶ፡ሁሉን፡እስከ፡ወሰደ፡ድረስ፡እንዳላወቁ÷የሰው፡ልጅ፡(የጌታ ኢየሱስ) መምጣት፡ደግሞ፡እንዲሁ፡ይሆናልና::

(የማቴዎስ፡ወንጌል፡24÷36-39)

## አስተዋይ ኖኅ የሰውን ዘር ያተረፈው በመርከብ ነበረ::

ዛሬም ሊመጣ ካለው የጥፋት አሳት ለማምለጥ ጊዜውም መንገዱም አለ::



ጊዜው ዛሬ ነው:: መንገዱ ጌታ ኢየሱስ ነው:: በእርሱ "ያመነ የተጠመቀም ይድናል÷ ያላመነ ግን ይፈረድበታል::"

(የማርቆስ ወንጌል 16÷16)

"በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፡ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም (በኢየሱስ) ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል ::" (የዮሐንስ ወንጌል 3÷18)

"ነገር ግን እላለሁ÷በመንፈስ ተመላለሱ÷የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ:: ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና÷እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም:: ... የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው:- እርሱም፡ ዝሙት÷ ርኩሰት÷መዳራት÷ጣዖትን ማምለክ÷ምዋርት÷ጥል÷ክርክር÷ቅንዓት÷ቁጣ÷አድመኛነት÷መለያየት÷መናፍቅነት÷ምቀኝነት÷መግደል÷ ስካር÷ዘፋኝነት÷ይህንም የሚመስል ነው:: ... እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም::" (ወደ ገላትያ ሰዎች 5÷16-21)

አንተስ? ተዘጋጅተሃል? ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ ታምናለህ:: ነገር ግን ኑሮህና ሕይወትህ በኖኅ ዘመን እንደነበሩት የሥጋህን ፍላጎት የተከተለ ነው? እግዚአብሔርን ለማምለክ ጊዜ ይወደድብሃል? የምትከተለው መንገድ የጥፋት መንገድ መሆኑን ልብህ እያወቀ የነፍስህን ነገር ችላ ብለሃል? ጌታ ዛሬም ይቀበልሃል:: ወደ እርሱ ተመለስ:: አንቺም::

## የንስሐ ፀሎት:-

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ÷ በልጅህ በኢየሱስ አምናለሁ:: ከዛሬ ጀምሮ አንተ ከማትወደው አኗኗር ርቄ እኖራለሁ:: ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በለኝ:: ከዛሬ ጀምሮ አንተን ለማወቅና ለመከተል እንድችል ርዳኝ:: ኢየሱስ ጌታዬና አዳኜ ነው:: ወደ መንግሥትህ ተቀበለኝ:: አሜን::

***ይህንን ፀሎት ከልብ ከፀለያችሁ በደብዳቤ አሳውቁን:: ተጨማሪ ጠቃሚ ምክሮችን ልንሰጣችሁ እንሞክራለን:: ***

በየጊዜው ያወጣናቸውን የደብዳቤ መልእክቶች በየትኛውም ክፍለ ዓለም የምትኖሩ ወገኖቻችን ማንበብ እንድትችሉ:- በዓለም አቀፍ ድረ ገጽ (world wide web) አቅርበናል:: አድራሻውም:-

www.ethioGodslove.org

## አስተያየታችሁን ጻፉልን::

እግዚአብሔር በልባችሁ በሚያመጣው መንገድ ሁሉ ተባበሩን:: በኢንተርኔት ደብዳቤአችንን ስትከፍቱ:-ጥቂት መታገሥ ይጠይቃል:: እንደ ኮምፒውተራችሁ ፍጥነት እስከ 1.5 ደቂቃ ሊያስጠብቅ ይችላል::

የጂቡቲ÷ የኬኒያ÷የሱዳን÷ የኤርትራ÷ የሊባኖስና የኢትዮጵያ አንባቢዎቻችን:- ደብዳቤአችንን ለብዙ አንባቢዎች መላክ እንድንችል÷አስተዋውቁን:: አድራሻዎችንም ላኩልን::

ይህንን መልዕክት በየ ቤተ ክርስቲያናቸው ደጃፍ÷በየሐበሻው ምግብ ቤትና ሱቆች በየወሩ በማስቀመጥ የሚተባበሩንን አገልጋዮች ጌታ እንዲያስነሣልን እየፀለይን ነው:: ፀልዩልን:: ትራክቶችንም ማቅረብ ይቻላል::

ኢየሱስ ጌታ ነው::
ጌታ ይባርክህ::